| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ርእስ ፡ አንቀጽ ። |
| ርእስ ፤ | "የዐላማ ፡ አንድነት!" |
| ደራሲ ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ። |
| ዕለት ፤ | መስከረም ፡ 2013 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፥ ቍ.2013-001 |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | |

# ርእስ ፡ አንቀጽ ።

editorial | éditorial | اِفْتِتاحي

## የዐላማ ፡ አንድነት!

እንኳን ፡ ከዘመነ ፡ ዮሐንስ ፡ ወደ ፡ ዘመነ ፡ ማቴዎስ ፡ በሰላም ፡ አሸጋገራችኹ! ፡ እያልን ፡ 2013 ፡ ዓ.ም. ፡ የሰላም ፤ የፍቅር ፤ የነጻነትና ፡ ያንድነት ፡ ዓመት ፡ እንዲኾንልን ፡ ከልብ ፡ እንመኛለን ።

የዐዲስ ፡ ዓመት ፡ ዋዜማ ፥ ኹል ፡ ጊዜም ፡ ቢኾን ፡ ለጥቅምና ፡ ጕዳት ፡ መተንተኛ ፤ ለጥፋትና ፡ ልማት ፡ መለያ ፤ ለሒሳብና ፡ ትርፍ ፡ ማወራረጃ ፤ ለነባር ፡ መዝገብ ፡ መዝጊያ ፤ ለዲስ ፡ መዝገብ ፡ መክፈቻ ፤ ለስሕተት ፡ ማስወገጃ ፤ ለልማት ፡ ማጠናከሪያ ፤ ለዐዲስ ፡ ዐቅድ ፡ ማቀጃ ፤ ለሥራ ፡ መነሻ ፡ ይውላል ።

በ2012 ፡ ዓ.ም. ፡ መባቻ ፡ እንደፈራነው ፥ ከድጡ ፡ ወደ ፡ ማጡ ፡ መንሸራተታችን ፡ ቀጥሎ ፥ ዛሬ ፥ በ2013 ፡ ዓ.ም. ፡ መባቻ ፥ ሀገሪቱ ፡ ከዓምና ፡ በባሰ ፡ አቋም ፡ እንደምትገኝ ፡ አረጋግጠናል ። ኾኖም ፥ «ነገር ፡ ከልኩ ፡ አያልፍም» ፥ እስካኹን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ የደረሰው ፡ በደል ፥ የበዳዮቿንም ፡ መቃብር ፡ ሲምስ ፡ ከርሞ ፥ እንሆ ፡ በ2013 ፡ ዓ.ም. ፡ መባቻ ፥ መቼም ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንገዱ ፡ አይመረመርም ፥ በመዘዘኛው ፡ "ኮሮና" ፡ ወቅት ፡ «ምርጫ ፡ አካኺዳለኹ!» ፡ «አታካኺድም!» ፡ በሚል ፡ መልክ ፡ በተጫረ ፡ ጠብ ፥ በዳዮቹ ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተከዳድተው ፡ ሲወነጃጀሉና ፡ ለጥፋት ፡ ሲፈላለጉ ፡ እናያለን ። መጠፋፋታቸው ፡ ገሀድ ፡ የኾነውን ፡ ያኽል ፥ ለሀገርና ፡ ለሕዝብ ፡ የሚተርፈው ፡ ያው ፡ ጥፋት ፡ መኾኑ ፡ ሳይታለም ፡ የተፈታ ፡ ነው ። የሀገር ፡ ባለቤት ፥ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብስ ፡ "የቤት ፡ ሥራውን" ፡ ከመሥራት ፡ ማን ፡ ከለከለው ፨ "ቀዳማዊ ፡ ደርግ" ፤ "ዳግማዊ ፡ ደርግ" ፤ "ሣልሳዊ ፡ ደርግ" ፤ ... ፡ እያለ ፡ የዐምባ ፡ ገነኖችን ፡ መተካካት ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ሲቈጥርና ፡ ሲታዘብ ፡ ይኖራል ፨ በ2013 ፡ ዓ.ም. ፡ «በቃ!» ፡ ሊላቸው ፡ ይገባል ፤ ለዚህ ፡ ግን ፡ አስቀድሞ ፡ የዐላማ ፡ አንድነት ፡ ሊኖረው ፡ ያሻል ።

የኀምሳ ፡ ዓመቱ ፡ የንኊልዮሽ ፡ ስብከት ፥ የሕዝቡን ፡ መንፈስ ፡ አንዴ ፡ በ"ኮምዩኒዝም" ፡ አንዴ ፡ በውልደት ፡ ደባልዮሽ ፡ (ethnic federalism) ፡ ሲበጠብጠውና ፡ ሲያተራምሰው ፤ ሲለያየውና ፡ ሲከፋፍለው ፡ ቈይቶ ፥ ዛሬ ፥ የጠራ ፡ የበራ ፡ አንድያ ፡ ሀገራዊ ፡ ዐላማውን ፡ እስካለማየት ፡ ያደረሰው ፡ መስሏል ።

ይህ ፡ አንድያ ፡ ሀገራዊ ፡ ዐላማው ፡ ሌላ ፡ አይደለም ፥ ሀገሩን ፡ ኢትዮጵያን ፡ በጧት ፡ በመሠረት ፡ ያቆመበት ፡ ሥልጣኔው ፡ ሥልጡንሕዝብናው ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ባዕድ ፡ አስተሳሰብ ፡ ወይ ፡ ፈሊጥ ፡ አይደለም ። የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የሚታገለው ፡ ሀገር ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለሰጠውና ፡ ላቈየለት ፡ ሥልጣኔው ፡ መኾን ፡ አለበት ፤ ይህን ፡ ሲፈጽም ፥ ድኅነቱን ፤ ነጻነቱንና ፡ እግዚእናውን ፡ በአንድነት ፡ ያገኛቸዋል ። ለሥልጡንሕዝብናው ፡ ሲታገል ፥ ጥንታዊ ፡ የግዛት ፡ ሥርዐቱን ፡ ያገኛል ፥ ያዘምነውማል ፤ ነጻነቱን ፡ ይዋጃል ፥ ክብሩን ፡ ይቀዳጃል ፤ ሰላሙንም ፡ ያረጋግጣል ፥ ጸጋዎቹንም ፡ ያጣጥማል ።

በመጪው ፡ ዘመን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ከጠላቶቹ ፡ የሚገላግለው ፥ የዐላማ ፡ አንድነቱን ፡ የሚሰጠው ፥ እግዚእናውን ፡ የሚያጐናጽፈው ፥ የእግዚአብሔር ፡ የምሕረት ፡ መንፈስ ፡ እንዲወርድለት ፡ ከልብ ፡ እንመኛለን ❉

እግዚእናችንን ፡ የማስከበር ፥
ሕገ ፡ መንግሥታችንን ፡ የመሥራት ፥
ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የርትዕ ፡ መንግሥታችንን ፡ የማቆም ፡
ሀገራዊ ፡ ዐላማችንን ፡ ለመፈጸም ፥ በኢትዮጵያና ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ የምንገኝ ፡ ሀገራውያን ፡ ኢትዮጵያውያን ፥ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካላችን ፡ ለኾነው ፡ ለኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ እናብር!
ኢ ሀ ሥ አ
የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ።
ሥልጡንሕዝብና ።
www.slttunhzb.net


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2013 ፡ ዓ.ም. ።